መልእክት አራት

## ኢዮብ እና ሁለቱ ዛፎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዘፍ. 2፥9፣ 17፤ ራእ. 22፥1-2፣ 14፤ ኢዮ. 1፥1፤ 2፥3፤ 42፥1-6

**I. በመለኮታዊው መገለጥ ውስጥ ሁለት ዛፎች፣ ሁለት ምንጮች፣ ሁለት መንገዶች፣ ሁለት መርሆች እና ሁለት መጠናቀቆች አሉ፡-**

ሀ. ሁለት ዛፎች፡-

1. የሕይወት ዛፍ ሰው ከሦስታንዱ አምላክ ጋር ባለው ግንኙነት ሦስታንዱ አምላክ ለሰው ሕይወት መሆኑን ያመለክታል—ዘፍ. 2፥9፤ መዝ. 36፥9።
2. የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ ሰው በእግዚአብሔር ፊት በመውደቁ ሰይጣን፣ ዲያብሎስ፣ ክፉው ለሰው ሞት መሆኑን ያመለክታል—ዘፍ. 2፥17።

ለ. ሁለት ምንጮች፡-

1. የሕይወት ዛፍ ለአቅርቦታቸው እና ለድሰታቸው እግዚአብሔርን እንደ ሕይወት ለሚሹ ሰዎች ምንጭ ነው—ዮሐ 1፥4፤ 15፥1።
2. የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ ወደ ሞትና የዘላለም ጥፋት ሰይጣንን እንደ መርዛቸው የሚከተሉ ሰዎች ምንጭ ነው—8፥44።
3. የእነዚህ ሁለት ምንጮች ውጤት ሁለት መንግሥታት ናቸው—የእግዚአብሔር መንግሥት እና የሰይጣን መንግሥት— ማቴ. 21፥43፤ 12፥26፤ ቆላ. 1፥13።

ሐ. ሁለት መንገዶች፡-

1. የመጀመሪያው መንገድ፣ እንደ አቅርቦት በዘላለማዊ ሕይወቱ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲፈልጉ፣ እግዚአብሔርን እንዲያገኙና እግዚአብሔርን እንዲደሰቱ ቀጭኑ መንገድ፣ የሕይወት መንገድ ነው—ማቴ. 7፥14፤ ሐዋ. 9፥2፤ 16፥17፤ 18፥25-26፤ 2 ጴጥ. 2፥15፣ 21።
2. ሁለተኛው መንገድ የሰይጣን ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሰዎች ሰይጣንን እንዲከተሉ ሰፊው መንገድ፣ የሞት እና የመልካምና ክፉ መንገድ ነው—ማቴ. 7፥13፤ 1 ዮሐ. 3፥10።

መ. ሁለት መርሆች፥-

1. የመጀመሪያው መርህ የሕይወት መርህ—በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ የመሆን መርህ ነው—ዮሐ. 15፥5፤ ዘፍ. 4፥4።
2. ሁለተኛው መርህ የሞት እና የመልካምና ክፉ መርህ—ከእግዚአብሔር ኢ-ጥገኛ የመሆን መርህ ነው—ኤር. 17፥5-6፤ ዘፍ. 4፥3።

ሠ. ሁለቱ መጠናቀቆች ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት የሚወስዷቸው የሁለቱ መንገዶች የመጨረሻ ውጤት ናቸው፡-

1. የእግዚአብሔር የሕይወት መንገድ መጠናቀቅ የሕይወት ውኃ ከተማ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት—ራእ. 21፥2፣ 10-11፤ 22፥1-2።
2. የሞት እና የመልካምና ክፉ መንገድ መጠናቀቅ የእሳት ባሕር ነው—19፥20፤ 20፥10፣ 14-15፤ 21፥8።

**II. የእግዚአብሔር ውጥን በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ መስመር ላይ ያለ ኢዮብ ሳይሆን በሕይወት ዛፍ መስመር ላይ ያለ ኢዮብ ይኖረው ዘንድ ነበር፡-**

ሀ. የኢዮብ እና የጓደኞቹ አመክንዮ በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ መስመር መሠረት ነበር—ኢዮብ 2፥11—32፥1።

ለ. ኢዮብ፣ እንደ ጓደኞቹ፣ የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ባለማወቅ በትክክልና በስህተት እውቀት ተይዞ ነበር—4፥7-8።

ሐ. ኢዮብና ጓደኞቹ በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ ክልል ውስጥ ነበሩ፤ እግዚአብሔር ከዚያ ክልል ሊያድናቸውና በሕይወት ዛፍ ክልል ውስጥ ሊያኖራቸው እየሞከረ ነበር—1፥1፤ 2፥3፤ 19፥10።

መ. ኢዮብን በማደቡ የነበረው የእግዚአብሔር ዓላማ እግዚአብሔርን በሙላት ያገኝ ዘንድ ከመልካምና ክፉ መንገድ ወደ ሕይወት መንገድ እርሱን ማዞር ነበር—42፥1-6።

**III. የሕይወት ዛፍ ራእይ—የእግዚአብሔር በክርስቶስ ምግባችን የመሆኑ ራእይ— ያስፈልገናል—ዘፍ. 2፥9፤ ራእ. 22፥1-2፤ 14፡-**

ሀ. የሕይወት ዛፍ ሦስታንዱ አምላክ በክርስቶስ፣ በምግብ መልክ እንደ ሕይወት ራሱን ወደ መረጣቸው ሰዎች ውስጥ ለማደል መሆኑን ያመለክታል—ዘፍ. 2፥9።

ለ. የሕይወት ዛፍ የአጽናፍ-ዓለም ማዕከል ነው፦

1. በእግዚአብሔር ዓላማ መሠረት፣ ምድር የአጽናፍ-ዓለም ማዕከል ናት፣ የዔድን ገነት የምድር ማዕከል ናት፣ የሕይወት ዛፍ የዔድን ገነት ማዕከል ነው፤ በመሆኑም፣ የአጽናፍ-ዓለም ማዕከል የሕይወት ዛፍ ነው።
2. ለእግዚአብሔር እና ለሰው ከሕይወት ዛፍ የበለጠ ማዕከላዊ እና ወሳኝ የሆነ ምንም ነገር የለም—3፥22፤ ራእ. 22፥14።

ሐ. ክርስቶስ የሕይወት ዛፍ ስዕል መፈጸም መሆኑን አዲስ ኪዳን ይገልጣል—ዮሐ. 1፥4፤ 15፥5።

መ. በዮሐንስ ወንጌል የተገለጡት ሁሉን-ያካተተው ክርስቶስ ገጽታዎች ሁሉ የሕይወት ዛፍ ውጤት ናቸው—6፥48፤ 8፥12፤ 10፥11፤ 11፥25፤ 14፥6።

ሠ. የሕይወት ዛፍ ድሰታ በእግዚአብሔር የተዋጁት ሁሉ ዘላለማዊ እድል ፈንታ ይሆናል—ራእ. 22፥1-2፣ 14፦

1. ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ለሰው የወጠነውን የሕይወት ዛፍ ለዘላለም ይፈጽማል—ዘፍ. 1፥26፤ 2፥9።
2. የሕይወት ዛፍ ፍሬዎች በእግዚአብሔር ለተዋጁ ለዘላለም ምግብ ይሆናሉ፤ እነዚህ ፍሬዎች በየወሩ በመፍራት ያለማቋረጥ ትኩስ ይሆናሉ—ራእ. 22፥2።

## IV. ዳግም ስንወለድ፣ ክርስቶስ ራሱን እንደ የሕይወት ዛፍ ወደ እኛ ውስጥ ተከለ—ዮሐ. 1፥12-13፤ 3፥3፣ 5-6፣ 15፤ 11፥25፤ 15፥1፣ 5፦

ሀ. በተግባራዊ ኑሮአችን፣ በመልካምና ክፉ እውቀት ዛፍ መስመር እንጂ በሕይወት ዛፍ መስመር ላይ ላንሆን እንችላለን—ምሳ. 16፥25፤ 21፥2።

ለ. ኢዮብ በስነ ምግባር ክልል ውስጥ ያለን ነገር ተከታተለ፣ እኛ በክርስቶስ ያለን አማኞች ግን በእግዚአብሔር ክልል ውስጥ ያለን ነገር ልንከታተል ይገባል—1 ቆሮ. 15፥28፤ ኤፌ. 3፥16-21።

ሐ. በየዕለት ኑሯችን ሕይወትን በሚሰጠው መንፈስ ክልል ውስጥ እንጂ በመልካምና ክፉ እውቀት ዛፍ ክልል ውስጥ መሆን የለብንም—1 ቆሮ. 15፥45፤ ሮሜ 8፥2።

መ. የእግዚአብሔር ውጥን ከእርሱ ጋር ፈጽሞ አንድ የሆንን ሰዎች እንሆን ዘንድ እኛን ማፍረስ እና እንደ ሕይወታችን እና ባሕሪያችን በራሱ መልሶ መገንባት ነው—2 ቆሮ. 1፥9፤ 4፥14።

© 2026 Living Stream Ministry